# ከእግዚአብሔር ፍቅር

“ … እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።” (ኢሳ 48 ÷ 17)

God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. አዘጋጅ መላኩ ትዕዛዙ E-mail – g l n l m @ethiogodslove.org

www.ethioGodslove.org ጥር 1997 1st Quarter 2005


ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ÷ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል። (ትንቢተ ኢሳይያስ 54÷13)



## ትክክለኛ ሥፍራ

(የኢግልስ ኔት ክርቲያኖች ሕብረት ቤተ ክርስቲያን መጋቢ የሆኑት÷ፓስተር ሪክ ጋድዊን፡- በአንድ ኮንፈረንስ ላይ ካስተማሩት መልክት የተተረጎመ።)

በትክክለኛው ሥፍራ መሆን÷ በሰው ሕይወት ፍሬያማነት ላይ ምን ያክል ኃይል እንዳለው ከእግዚአብሔር ቃል እንመልከት። የሚከተለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በምታነቡበት ጊዜ (ሥፍራ÷ እዚያና በዚያ) በሚሉት ቃላት ላይ ትኩረት አድርጉ።

ኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 12

ቁጥር 1. “በምድር ላይ በምትኖሩበት ዘመን ሁሉ የአባቶቻችሁ አምላክ እግዚአብሔር ለመውረስ በሰጣችሁ አገር÷ የምትጠብቁአትና የምታደርጉአት ሥርዓትና ፍርድ እነዚህ ናቸው።”

ቁጥር 5. “ነገር ግን አምላካችሁ እግዚአብሔር ከነገዶቻችሁ ሁሉ ስሙን በዚያ ያኖር ዘንድ ወደዚያ ወደ መረጠው ሥፍራ ትመጣላችሁ÷ማደሪያውንም ትሻላችሁ።

6. ወደዚያም የሚቃጠለውን መሥዋዕታችሁን÷ሌላ መሥዋዕታችሁንም÷አሥራታችሁንም÷በእጃችሁም ያነሣችሁትን ቍርባን÷ ስእለታችሁንም÷ በፈቃዳችሁ የምታቀርቡትን÷የላማችሁንና የበጋችሁንም በኵራት ውሰዱ። 7. በዚያም በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ፊት ብሉ÷እጃችሁንም በምትዘረጉበት ÷ አምላክህ እግዚአብሔር በባረከህ ነገር ሁሉ÷ እናንተና ቤተ ሰባችሁ ደስ ይበላችሁ።” 8. ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን÷... ሁሉ አታደርጉም” ይላል።

ወገኖቼ፡- ሁሉም በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን የሚደርግበት እንደዚህ ያለ ትውልድና ዘመን ኖሮ የሚያውቅ አይመስለኝም። እስቲ ቀጥለን እናንብብ፡-

ቁጥር “9. አምላካችሁ እግዚአብሔር ወደ ሚሰጣችሁ ዕረፍትና ርስት እስከ ዛሬ ድረስ አልገባችሁምና። 10. ዮርዳኖስን ግን በተሻገራችሁ ጊዜ÷አምላካችሁም እግዚአብሔር በሚያወርሳችሁ ምድር በተቀመጣችሁ ጊዜ፡ያለ ፍርሃትም እንድትኖሩ ከከበቡአችሁ ጠላቶች ሁሉ ዕረፍት በሰጣችሁ ጊዜ÷...”

እዚህ ላይ ደግሞ የውርስ ሥፍራና ያለፍርሐት መኖር ተጣምረው ይገኛሉ፡ እስራኤል ያለ ፍርሐት ለመኖር በውርሱ ሥፍራ መሆን እንዳለበት ያመለክታል። ጌታ በወሰነው ጥሪና ሥፍራ ሲኰን ጥበቃው አውቆ የሚከተል ፈቃዱ ስለ ሆነ ነው፤ እግዚአብሔር ይመስገን።

“11. አምላካችሁ እግዚአብሔር ስሙ ይጠራበት ዘንድ ወደዚያ ወደ መረጠው ሥፍራ እኔ የማዛችሁን ሁሉ÷የሚቃጠለውን መሥዋዕታችሁን÷ሌላ መሥዋዕታችሁንም÷ አሥራታችሁንም÷ በእጃችሁ ያነሣችሁትንም ቍርባን፡ለእግዚአብሔር ተስላችሁ የመረጣችሁትን ስእለታችሁን ሁሉ ውሰዱ። 13. የሚቃጠለውን መሥዋዕትህን በሚታይህ ሥፍራ ሁሉ እንዳታቀርብ ተጠንቀቅ። ነገር ግን እግዚአብሔር ከነገዶችህ ከአንዱ ዘንድ በመረጠው ሥፍራ ፤ በዚያ የሚቃጠለውን መሥዋዕትህን አቅርብ÷በዚያም የማዝዝህን ሁሉ አድርግ። 17. የእህልህን የወይን ጠጅህን የዘይትህንም አሥራት÷የላምህንና የበግህንም በኵራት÷የተሳልኸውንም ስእለት ሁሉ÷በፈቃድህም ያቀረብኸውን በእጅህም ያነሣኸውን ቍርባን በደጅህ ውስጥ መብላት አትችልም።

18. ነገር ግን አንተ÷ ወንዶችና ሴቶች ልጆችህም÷ ባሪያዎችህና ገረዶችህም÷ በአገርህም ደጅ ያለው ሌዋዊ አምላክህ እግዚአብሔር በመረጠው ሥፍራ በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት ብሉት፤ 26. ነገር ግን የተቀደሰውን ነገርህን ስእለትህንም ይዘህ እግዚአብሔር ወደ መረጠው ሥፍራ ሂድ። 28. በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት መልካምና ቅን የሆነውን ነገር ስታደርግ ለአንተ ከአንተም በኋላ ለልጆችህ ለዘላለም መልካም ይሆንላችሁ ዘንድ እኔ የማዝዝህን እነዚህን ቃሎች ሁሉ ሰምተህ ጠብቅ”ይላል። አያችሁ? በትክክለኛ ሥፍራ መሆን ለራስ ብቻ ሳይሆን ለልጅም የሚተርፍ ነው።

---

በትክክለኛው ሥፍራ ስለ መሆን ሰባት መርሆዎችን ላሳያችሁ። ምንም ያክል ጥሪ ቢኖራችሁ÷ የተቀባችሁና የተማራችሁ ብትሆኑና÷ ነገር ግን እግዚአብሔር በወሰነላችሁ ሥፍራ ባትሆኑ÷ብሩክና ፍሬያማ አትሆኑም። ምክንያቱም ኣለመታዘዝ ስለሚሆንባችሁ ነው። ኣለመታዘዝ፡- ደግሞ አንድም ባለማስተዋል÷ ኣለዚያም እያወቁ በራስ ፍላጎት በመሄድ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ሰው ያለ ሥፍራው በመሆን የሚጎድልበትና የሚቀርበት ነገር በቀላሉ ሊወሰድ አይገባም። ስለዚህ ሰባቱን መርሆዎች አስቲ እንመልከት።

### 1. ነፍስ ሁሉ በተገቢ ሥፍራዋ ትሆን ዘንድ የእግዚአብሔር ዓላማ ነው

በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ÷እግዚአብሔር ሰውን እንደ ፈጠረ እናነባለን። በምዕራፍ 2÷8 ደግሞ “እግዚአብሔር አምላክም በምሥራቅ በዔድን ገነትን ተከለ፡የፈጠረውንም ሰው ከዚያው አኖረው” ይላል። ይህም የሚያመለክተው አዳም በገነት ውስጥ እንዳልተፈጠረና ጌታ ከፈጠረው በኋላ÷ወስዶ በገነት እንዳኖረው ነው። ከዚህም የምንረዳው እግዚአብሔር በተገናኘን ሥፍራ እንደማይተወን ነው። በእግዚአብሔር ዓላማ መሠረት ለእያንዳንዳችን ትክክለኛ የሆነ ጥሪና ሥፍራ አለ።ሥፍራችንንም የሚወስነው ጥሪው ነው። የአዳም ጥሪ (የሕይወቱ ዓላማ) ገነትን መንከባከብና መጠበቅ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ ወደ ትክክለኛ ሥፍራው ወስዶ በገነት አኖረው፤ ስሙ ይክበር።

የሰው ሕይወት በፍሬና በስኬት እንዲባረክ የእግዚአብሔር ፍላጎት መሆኑን እናውቃለን። ነገር ግን ይህ ሊሆንለት የሚችለው÷ በተገቢው ሥፍራ÷ ሲሆን ብቻ ነው። የአዳም ሕይወት በገነት ውስጥ እንዴት ፍሬአማ እንደ ነበረ እናውቃለን። ከገነት ከተባረረ በኋላ ግን “ጥሮ ግሮ” መኖር ግዴታው ሆነ። ዛሬም እንደዚሁ ነው። ለእያንዳንዳችን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ትክክለኛ ሥፍራ አለ፤ እግዚአብሔር ይመስገን። አሁን ያለኸው በሥፍራህ ከሆነ÷እንዳትለቅ ተጠንቀቅ። ካልሆነም÷ረግተህና ጸንተህ፡ዋጋ በመክፈል፡- በመክሊትህ የምታገለግልበትን ሥፍራህን_ እንዲያሳይህ ተግተህ ጸልይ።

ጌታ ሁሉንም ነገር በሥርዓት÷በየሥፍራው አድርጎታል። ፀሐይን÷ ጨረቃንና ከዋክብትን ሁሉ ጠቃሚ ሊሆኑ በሚችሉበት በመደበላቸው ሥፍራ አኑሮአቸዋል። አንተንም በደሙ ከዋጀህ በኋላ በአካሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሰበልህ ሥፍራ አለልህ። ስለዚህ ራስህን በፈቀድኸው ሥፍራ ማስቀመጥ አትችልም። ባመቸህም ሥፍራ ሁሉ መሆን አልተፈቀደልህም። በፈቃድህም ራስህን ካስቀመጥህ÷ በሚገጥምህ ሁኔታ ሁሉ ራስህን መቻል ይኖርብሃል። ጌታ ጠርቶ ባስቀመጠህ ሥፍራ ከሆንህ ግን በሚገጥምህ ሁኔታ ሁሉ ራሱ እግዚአብሔር ሊጠነቀቅልህ የታመነ ነው።

በዚህ ዘመን “በነፃነት” የሚመላለሱ ብዙ “እንደልቡዎችና እንዳሻውዎች” በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሞልተዋል። ከክፍለ ሐገር ወደ ክፍለ ሐገር የሚዘልሉ፡ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚምዘገዘጉ÷በአንድ ቦታ ጸንቶ እግዚአብሔርን መጠበቅና ማደግ አስፈላጊነቱ የማይታያቸው ዘላን ክርስቲያኖች የበዙበት ዘመን ነው። እነዚህ ሰዎች ምቹ ብለው በገመቱበት ሁሉ የሚቀመጡት በራሳቸው ፈቃድ ስለ ሆነ÷ ምን ጊዜም ደስተኞች አይሆኑም። በቀላሉ ይከፋሉ። ጌታም ስላላስቀመጣቸው የሚደገፉበት ጸጋው የላቸውም። ስለዚህ ደጋግመው ተነሥተው ለመሄድ ይገደዳሉ። በጥሪና በምሪት ሳይሆን በምቾት ይነዳሉ ማለት ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔር ተቀዳሚ ዓላማ ነፍስ ሁሉ በተገቢ ሥፍራዋ ትሆን ዘንድ ነው። ክብር ለስሙ ይሁን።

### 2. በተገቢው ሥፍራ መሆን መለኰታዊ ርዳታንና ጥበቃን ያስከትላል።

በመጽፈ ነገሥት ቀዳማዊ 17 እንደተጻፈው በገለዓድ የነበረው ቴስቢያዊው ነቢዩ ኤልያስ÷በአክዓብ ግዛት ውስጥ ዝናብ እንዳይዘንብ ተነበየ። ከዝናብም እጦት የተነሣ ታላቅ የኢኮኖሚ ችግርና

ርሃብ በሐገሪቱ ሰፈነ። ሕዝቡም ያለ አን ዳች ተስፋ ሞቱን ይጠባበቅ ነበረ። ነቢዩ ኤልያስ ግን፦ "የእግዚአብሔር ቃል እን ዲህ ሲል ለእርሱ መጣለት፦ከዚህ ተነሥተህ ወደ ምሥራቅ ሂድ፥በዮርዳኖስም ትይዩ ባለው በኮራት ፈፋ ውስጥ ተሸሸግ። ከወ ንዙም ትጠጣለህ፥ቍራዎችም በዚያ ይ መግቡህ ዘንድ አዝዣለሁ። ሄደም እንደ እግዚአብሔር ቃልም አደረገ።... ቍራ ዎቹም በየጥዋትና በየማታው እንጀራና ሥጋ ያመጡለት ነበር፤ከወንዙም ይጠጣ ነበር" (መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 17፥2-6)

ከዚህ ምን እንረዳለን? ኤልያስ ተነሥቶ ወደ ትክክለኛው ቦታ መሄድ እንዳለበት ነው። እርሱም ጌታ ወዳዘጋጀለት ሥፍራ ከሄደና ፥ በዚያም መቆየት የሚገባውን ያክል ከቆየ፥የሚያስፈልገው ጥበቃና ቀ ለቡ አይጎድልበትም ማለት ነው። ነገር ግን ነቢዩ እንዳሻው ቢሄድና ባሰኘውም ሥፍራ ቢቀመጥ ኖሮ፥ በርሃብ በሞተ፥ ወይም ጠላቶቹ ፈቃዳቸውን ባደረጉበት ነበር።

ቀጥሎም፥ በዚሁ ምዕራፍ በቁጥር 7፥8 እና 9 ስንመለከት፦እንዲህ ይላል።"ከብ ዙ ቀንም በኋላ በምድር ላይ ዝናብ አል ነበረምና ወንዙ ደረቀ። ተነሥተህም በ ሲዶና አጠገብ ወዳለችው ወደ ሰራፕታ ሂድ፥በዚያም ተቀመጥ፤እነሆም፥ ትመግ ብህ ዘንድ አንዲት ባልቴት አዝዣለሁ፤ የሚል የእግዚአብሔር ቃል መጣለት።" መታዘዝ ልማዱ የሆነው የእግዚአብሔር ሰውም ተነሥቶ ወደ ሥፈራው ሄደ። እግዚአብሔርም እንደ ቃሉ አደረገለት፤ ስሙ ይክበር። ከነቢዩም መታዘዝ የተነ ሣ፥ እርሱ ብቻ ሳይሆን ባልቴቷና ልጅ ዋም ጭምር አንድም ቀን ሳይራቡ ክፉ ውን ጊዜ አለፉት፤እግዚአብሔር ይመስ ገን። ስለዚህ በትክክለኛ ሥፍራ መሆን የእግዚአብሔርን ረድኤት ያስከትላል።

በአንድ ሥፍራ በጸጋና በታላቅ ቅባት ያገለግሉ የነበሩ ሰዎች፥ጌታ ሳይመራቸ ው፥ተነሥተው ወደ ሌላ ሥፍራ ወይም ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ሲሄዱ፥ በድን ገት የጸጋው ምንጭ ይደርቅባቸውና፥ ጥሪያቸው ይከሽፋል። ከብዙ ዓመታት በፊት አውስትራሊያ በሄድሁ ጊዜ፦ ዳር ሊን ቼክ፥ የተባለው ታዋቂ ሙዚቀኛ በወጣቶች አገልግሎት ውስጥ ተራ ረዳ ት ነበር። ብራያን ሕውስተን ደግሞ ም ንም ዝና ወይም መልክና ቁመና ያልነበ ረው፥ ተራ ሰው ነበረ። ሁለቱም ምንም ታዋቂነት አልነበራቸውም። ሆኖም እነ ዚሁ ተራ ሰዎች ያወጡዋቸው ተወዳጅ መዝሙሮች፥ዛሬ በመላው ዓለም የታወ ቁና የተደነቁ ናቸው፤ ብዙ ገንዘብም አስገብተዋል።

ነገር ግን እነዚህ መዝሙሮች በተደረ ሱበት ሥፍራ በመጀመሪያ የተመረጠው ዳርሊን ቼክ አልነበረም። የመጀመሪያው ምርጫ የነበረውና አገልግሎቱም ሲመ ሠረት ከብራያን ጋር አብሮ የነበረው ሰ ው ሌላ ነበረ። ያም ሰው በሙዚቃ ጸጋና በሞገስ ያገለግል ነበር። የእግዚአብሔርም ክብር በዚያ ሊገለጥ ጊዜውን ይጠባበቅ ነበር።

ብራያን መዘመርም ሆነ ሙዚቃ መድ ረስ አይችልም።ስለዚህ ያንን ሰው በዚያ ሥፍራ ያስቀመጠው ጌታ መሆኑ ይታወቅ ነበር። ያም ሰው መዝሙሮችን በመድረስ ያገለግል ነበር። ሥፍራውም ስለ ነበረ የጌታ ውበት ነበረው። ሆኖም ከዕለታት አንድ ቀን በልቡ፥ ትዕቢት አደረበትና በቀላሉ መቀየም ጀመረ። ከዚያም ብራ ያንን ትቶ ለመሄድ መረጠ። ዓላማውም ያንን የሙዚቃ አገልግሎት ይዞ መሄድ ነበር።ምክንያቱም፥ እርሱን የሚያክል ሙዚቀኛ በዚያ ስላልነበረ ነው። በጌታ ወንድሞቹ የሆኑት እንዲቆይላቸው ለመ ኑት፥ ተለማመጡትም እርሱ ግን ዘራፍ ብሎ ሄደ። ያም ሰው ከሙዚቀኞቹ መለ የት ብቻ ሳይሆን ሚስቱንም ትቶ ከሌላ ሴት ጋር መሄድ ጀመረ። በመጨረሻም ሚስቱን ፈትቶ ሌላኛይቱን ሴት አገባ።




እነሆ፥ይህ ከሆነ ዓመታት አልፈዋል። ሆኖም ዛሬ ያንን ሰው የሚያስታውሰው የለም። ሰውየው አሁንም አለ። ያ ሁሉ ችሎታውም የትም አልሄደም።ዕውቀቱ ም እንዳለ ነው። ነገር ግን ያ ሰው ሁለ ተኛ አይታወስም። እግዚአብሔር አሁን ም ይወደዋል። በንስሐ ቢመለስ ጌታ ይ ምረዋል። እርሱ ግን ንስሐ ገብቶ አያው ቅም። ስለዚህ ሊነግ አልቻለም። ስለዚህ ም፥እርሱ በትዕቢት ትቶት የሄደው አገ ልግሎት ዛሬ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲከብ ር እያየ፥ በቁጭት ይቃጠላል ብየ እገም ታለሁ። ወገኖቼ ጌታ ከዚህ ያድነን።

አስቴር እምቢተኛዪቱን ንግሥት አስ ጢንን እንደ ተካች፥ ያ ሰው በክብር ሊ ያገለግል የተጠራበት ያ አገልግሎት ለ ሌላ ትሑትና ታዛዥ ሰው ተላለፈ። ይህ ም ታማኝና ታዛዥ ሰው እግዚአብሔር ባስቀመጠው ሥፍራ ታግሶ ከመቆየቱ የተነሣ የክብር መገለጫና የበረከቱ ተካ ፋይ ሊሆን ቻለ። ስለዚህ፥ በምንም ምክ ንያት፥ልብህ አብጦብህ፥ ማኩረፍ ብት ጀምርና እግዚአብሔር ካስቀመጠህ ሥ ፍራ ለቅቆ መሄድ ቢከጅልህ፦ምናልባት ራስህን ከሥፍራህ በመንቀል፥ ከጌታ ፈ ቃድና ከበረከቱ ጋር እንዳትተላለፍ እፈራልሃለሁ።

በደቡብ አፍሪካ፥ደርበን በሚባል ከተ ማ አንድ ወዳጅ ነበረኝ። እርሱም የታላ ቅ ቤተ ክርስቲያን መሪ ነበረ። የተቀባ ሰባኪና ብዙ ነፍሳትን ለጌታ የማረከ፥እን ግዳ ተቀባይ የፍቅር ሰው ነበረ። አገልግ ሎቱም በሁሉ የተባረከ ነበረ።

እርሱም "እግዚአብሔር ወደ አሜሪካ እንድሄድ ይፈልገኛል" እያለ ይነግረኝ ነበር። እኔም ሃሳቡ መልካም ሆኖ አልታ የኝም። ሆኖም ልቃወመው ድፍረት ስላ ልነበረኝ፥ ርግጠኛ ነህን? ከወንድሞችስ ተማክረሃልን? አሜሪካ ትልቅ ሃገር ስለ ሆነ፥ ብዙም አገልጋዮች ስላሉት፥ ጌታ በግልጽ ካልጠራህ በቀር፥ ባትሄድ ይሻላ ል፥ ከማለት አላለፍሁም። ትልቅ ሰው በመሆኑ ልደፍረው ስላልቻልሁ ነው እን ጂ ብከለክለው ደስ ባለኝ ነበር። እርሱ ግን ጌታ እንደ ቀድሞው ይባርከኛል ሲል፥ በድፍረት ተነሥቶ ወደ አሜሪካ ሄደ። እኔም እያዘንሁለት በልቤ፥ከአንድ ዓመት በኋላ የሚያስታውስህ እንኳ ቢገኝ ታድ ለሃል አልሁት። እርሱም ወደ አሜሪካን መጥቶ እስከ ዛሬ ድረስ፥ መቶ ሰው እንኳ የሌለው ቤተ ክርስቲያን መሪ ሆኖ እየ ተፍጨረጨረ ይኖራል። የቤተ ክርስቲያ ኑ ገቢ ሊያስተዳድረው ስለማይችል፥ባለ ቤቱ የሕንፃ ሻጭ ደላላ ሆና በመሥራት ትደግፈዋለች።

አያችሁ፦ለአፍሪካ የተሰጠውን የተሳካ የእግዚአብሔር ጥሪ፥እንዳሻው ወደ አሜ ሪካ ማስተላለፍ የሚችል መሰለው።ነገር ግን ራሱ እግዚአብሔር ፥ ካልፈቀደና በግልጽ ካልመራ በቀር አይቻልም። ወዳ ጄ ምንም አልተለወጠም። ቅባቱም፥ጸጋ ውም፥ጥሪውም እንዳለ ነው። ሥፍራው ብቻ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ስለ ሆነ፥ አገልግሎቱ ተጨናገፈ። ይበልጥ የሚያሳዝነው ደግሞ በንስሐ ወደ መጣ በት አለመመለሱ ነው። መቼም ሰው ሆ ኖ የማይሳሳት የለም።ከተረዱ በኋላ አለ መታረም ግን ይበልጥ ያሳዝናል። በመን ታ መንገድ ላይ፥ተሳስቶ የማያዋጣ አቅ ጣጫ የወሰደ ሰው ተመልሶ አቅጣጫው ን ያርም የለ? ወገኖቼ፦ ከሳትን ለመታ ረም ትኅትናም ድፍረትም ቢኖረን መል ካም ይሆንልናል። ተመልሰንም በተገቢው ሥፍራ በመሆን በእግዚአብሔር ረድኤት ውስጥ ማገልገል ይቻለናል። ያለ ሥፍራ መሆን ግን የጌታ ረድኤት እንዳይመጣ መንገዱን ይዘጋል።

ፋሲካን አታስታውሱም? የሞት መላክ የግብፅን በኩር ለመግደል በመጣበት ጊ ዜ፥ደም በበሩ ላይ ባለበት (ሥፍራ) ላሉ ት ሁሉ የእግዚአብሔር ልዩ ጥበቃ ነበረ በዚያን ወቅት መንሽራሽር ያማረው ቢኖ ር ግን፥የሞት መላክ ሰይፍ እራት ይሆን ነበር እንጂ ጥበቃ አይኖረውም። ምክን ያቱም ጥበቃው የተፈቀደው፦ ደሙ በተቀባባቸው ቤቶች ውስጥ ብቻ ስለ ነበረ ነው።

## 3. በተገቢው ሥፍራ መሆን የራስን ምቾትና ክብር መካድ ይጠይቃል

እግዚአብሔር ባስቀመጠን ሥፍራ እንዳ ንጸና ከሚያደርጉን ነገሮች አንዱ ትዕቢት ነው። መጽሐፍ እንደሚል፥ እግዚአብሔር ትዕቢተኛን ይቃወማል። ለትኁታን ግን ጸጋን ያበዛል። ስለዚህ ጌታ ባስቀመጠን ሥፍራ ለመጽናት ትኁት መሆን ያስፈ ልጋል።



እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በሚመቸን መንገድ አይረዳንም። ለምሳሌ ነቢዩ ኤልያስ አይሁዳዊ ሆኖ ሳለ፥ በርኩስነቱ ከታወቀው ከቍራ ተቀብሎ መመገብ ነበረበት። በትዕቢት ዘራፍ ቢል ኖሮ ግን ያለ ቀኑ በርሐብ በሞተ ነበረ።ነቢዩ ግን ምንም ጥሩ አይሁዳዊ ቢሆንም፥ ራሱን አዋርዶ፥እግዚአብሔር በፈቀደው መንገ ድ የላከውን ርዳታ የመቀበል ጸጋ ነበረ ው። ውጤቱም፥ የአምላኩ ፈቃድ በሙ ላት በሕይወቱ መከናወኑ ነው። እግዚአ ብሔር ይመስገን።

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ኤሊያስ የነበረበ ት ሥፍራ ምንጩ ስለ ደረቀ፥ጌታ ወደ አንዲት ድኃ ባልቴት ላከው። እርሱም

ትዕቢተኛ ቢሆን ኖሮ ፥ የእግዚአብሔር ታላቅ ነቢይነቱን በመቁጠር፥"ከአንዲት ድኃ ባልቴት ርዳታ እንዴት እቀበላለሁ" ሊል በቻለ ነበር። በትዕቢት ምክንያት፥ ምክር እንኳን የማይቀበሉ ሰዎች አሉ። ርዳታን ሆነ የማይገባቸውን ነገር ለመረዳት የማይጠይቁ ትዕቢተኛ ክርስቲያኖች ብዙ ናቸው። *ነገር ግን በተገቢው የእግዚአብሔር ሥፍራና ዓላማ ውስጥ ለመኖር ትኅትና ግዴታ ነው።*

## 4. ወደ ትክክለኛው ሥፍራ መድረስ አብዛኛውን ጊዜ፥ በማይመች ሁኔታ ውስጥ ያሳልፋል፡

ሰው፥ምቾት ወዳጅ ፍጥረት ስለ ሆነ፥ ከነበረበት ሥፍራ ወጥቶ ወደ ተገቢው ሥፍራ ለመግባት እንዲጨክን፦ ያለበት ሁኔታው ፈጽሞ የማይመች መሆን አለበት። የንስር እናት፥ልጆቿ ለመብረር ዕድሜ ሲደርሱ፥ጎጆአቸውን ታፈርሳለች አሉ። በጫጩትነት ወራት የተሠራላቸውን ጉዝጓዝ ሁሉ ታስወግዳለች አሉ። ይህንንም የምታደርገው ልጆቿ የለመዱትን ምቾት ሲያጡ፥በረራን የመማር ግዴታ እንዲሰማቸው ለማድረግ ነው። እግዚአብሔርም አንዳንድ ጊዜ እንደዚሁ በማይመቹ ሁኔታዎች ውስጥ እንድናልፍ ይፈቅዳል። ይህም መልካም እንዲሆንልንና ወደ ፊት ለመዘርጋት ጉልበት እንዲሆንልን እንጂ እንድንጎዳ አይደለም፡ ስሙ ይክበር።

## 5. በትክክለኛ ሥፍራ መሆን ለአገልግሎት ፍሬና ለእግዚአብሔር ክብር መገለጥ እጅግ ወሳኝ ነው።

በኦሪ ዘጸአት፥እግዚአብሔር ሙሴን፦ "በመካከላቸው አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ" ባለ ጊዜ፥ "እኔ እንደማሳይህ ሁሉ ፥ እንደ ማደሪያው ምሳሌ ፥ እንደ ዕቃውም ሁሉ ምሳሌ፥ እንዲሁ ሥሩት" ነበር ያለው። (ዘጸአት 25፥9) መሰውያውም በተሰጠው መመሪያ መሠረት ተሠራ። ዛሬ ግን ሁሉም መከራውን የምያበዛው፥ እግዚአብሔር የሰጠውን መመሪያ አስተውሎ ባለመከተል ነው። የሙሴው መሰውያ በጌታ መመሪያ መሠረት በትክክል ከተከናወነ በኋላ፥ ካሕናቱም ሁሉ <u>በትክክለኛ ሥፍራቸው</u> ከቆሙ በኋላ፥ምን ሆነ? <u>"ደመናውም የመገናኛውን ድንኳን ከደነ፥ የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ሞላ</u>።" እግዚአብሔር ይመስገን።
(ኦሪት ዘጸአት 40፥34)

ከብዙ ዓመታት በኋላ የሰለሞን መቅደስ ሲሠራም እንዲሁ ነበር የሆነው። ሰሎሞን መቅደሱን <u>በእግዚአብሔር ቃል መሠረት በትክክል አስሠርቶ ፈጸመ</u>። በምረቃውም ዕለት እንዲህ ሆነ፦ "<u>ሰሎሞንም ጸሎቱን በፈጸመ ጊዜ እሳት ከሰማይ ወርዶ የሚቃጠለውን መሥዋዕትና ሌላ መሥዋዕቱን በላ ፤ የእግዚአብሔርም ክብር ቤቱን ሞላ</u>።" ክብር ለስሙ ይሁን። (ዜና መዋዕ ካልዕ 7፥1) ይህ ሁሉ ክብር ከመገለጡ በፊት ግን ሁሉም ነገር በተገቢው ሥፍራና አኳኋን መገኘት ነበረበት።

ዛሬም የእግዚአብሔር ክብር ሊገለጽ ዝግጁ ነው። ነገር ግን የሚያግደው አለ፡ እርሱም ሁሉም ነገር፥ በቃሉ መሠረት፥ ሥፍራውን አለመያዙና አለመዘጋጀቱ ነው። አንድ ከባድ ነገር ልጠቁምህ፦ *በሕይወትህ ምንም እንቅስቃሴና ፍሬ የማይታይ ከሆነ፥ ያለሥፍራህ ልትሆን ትችላለህ።* <u>የሕይወትህን ጥሪ እያከናወንህ ነህ? በትክክለኛው ሥፍራህስ ነህ?</u> ስለ መልካም አድራጎት ሳይሆን፥ የተጠራህበትን ኃላፊነት በመወጣት ላይ ነህ ?

ዛሬ፥ቤተ ክርስቲያን፥የሕይወቱን ዓላማ በማያስተውል፥ምቾት አሳዳጅና በቀላሉ አኵራፊ በሆነ፥ ምክርና ተግሣጽ በማይመልሰው ትውልድ ጤናዋ እየተቃወሰ ነው። ይህም ቶሎ ልንነቃበትና ልናርም የሚገባን ዘመናዊ ችግር ነው።

ትችት ታዘወትራለህ? በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ፥ ከለማው ይልቅ የጠፋው ጎልቶ ይታይሃል? የራስህ አገለግሎት ከሁሉ በልጦ ይሰማሃል? ወገኖቼ አይወዱኝም፥አያከብሩኝም፥ብለህ ትነጫነጫለህ? መፍትሔው ሁለት ነው። አንድም <u>ሥፍራህን ፈልግ</u>፥አለዚያም <u>ዓይኖችህን ወደ ራስህ መልሰህ ታረም</u>። በቀረው ግን ሥፍራዬ ብሎ፥በሰላምና በትኅትና ለማገልገል የተሰማራውን ሕዝበ እግዚአብሔር ለማወክ፥ ከሴይጣን ጋር ለምን ትተባበራለህ? ይህ ከአንተ/ቺ ይራቅ።

## 6. በትክክለኛ ሥፍራ አለመሆን ለፈተናና ለኃጢአት ያጋልጣል

አዳም ኃጢአት ባደረገበት ጊዜ ጌታ በመጀመሪያ "ወዴት ነህ?" በማለት የጠየቀው ያለበትን ሥፍራ ነበር። በኃጢአቱ ምክንያት በተለይ ለእርሱ ከተዘጋጀለት ሥፍራ መልቀቅ ግድ ሆኖበት ነው፡ ወገኖቼ፥በትክክለኛው ሥፍራችን ካልሆንን፥ የእግዚአብሔርን ክብር መገለጥ አናይም። የልቁንም ደግሞ ለክፉ ፈተናና ለኃጢአት እንጋለጣለን።



ነቢዩ ዮናስ ጌታ ወደ ምዕራብ፥ ወደ ነነዌ ልኮት እያለ፥ወደ ምሥራቅ የሚጓዝ መረከብ መሳፈሩ ምን ማድረጉ ነበር? ታሪኩን እንደምታውቁት ፥ ነቢዩ ዮናስ እግዚአብሔር ወዳዘዘው ሥፍራ ሄዶ ቢሆን ኖሮ ያ ሁሉ አውሎ ነፋስ ባልመጣ፡ ዓሣ ነባሪውም ባልዋጠው ነበር። የመርከብ ተጓዦችም ያለበደላቸው ባልተጉላሉ፥ ነቢዩም ሦስት ቀንና ሌሊት ተቀብሮ ባልኖረ ነበር። ለመሆኑ፥ ዛሬ በዓሣ ነባሪ ሆድ ተዘግቶበት፥ያለሥፍራው የተቀመጠ፥ ስንት ነቢይ ይኖር ይሆን? ስንቱስ ይሆን ያለአቅጣጫው መርከብ ተሳፍሮ በመጓዝ፥ ለመንገደኞች መታወክ ሰበብ የሆነ? ስንቱስ ይሆን ጌታ ባርኮ ባስቀመጠው ቦታ አርፎ እንደ ማገልገል ሥፍራውን ለመልቀቅ የሚቁነጠነጥ? እግዚአብሔር ከዚህ የዘመኑ በሽታ ይፈውሰን።

---

በመጽሐፈ ሩት ምዕራፍ አንድ እንደ ተጻፈው፥አቤሜልክ የኑኃሚን ባል፦ ቤተ ሰቡን ይዞ በሞዓብ ሊቀመጥ ከቤቴልሔም ወጥቶ ሄደ። ያም በአይሁዳዊነቱ ያልተፈቀደ ነበር። በዚያም ሳይቆይ ሞተ። ልጆቹም ሞቱ። ሴቶቹም ለብቻቸው ቀሩ። ኑኃሚንም በእፍረትና በሐዘን ወደ ቤተልሔም ከሩት ብቻ ጋር ተመለሰች። ወገኖቼ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ተነሥቶ በመሄድ፥ በራስ ብቻ ሳይሆን በቤተሰብም ላይ መፍረድ እንደሚቻል ላሳስባችሁ እወዳለሁ።

ሎጥ መጀመሪያውንም ከአብርሃም ጋር መሆን አልነበረበትም። አብርሃም ከዘሩ ከዘመዶቹም ተለይቶ እንዲሄድ እንጂ አጎቱን ይዞ እንዲሄድ አልተጠራም ነበር። ነገር ግን አብርሃም፥በጥሪው ውስጥ የሌለን ሰው አብሮ በመውሰዱ ፥ ሎጥ ቤተሰቡን ሊያጣ ቻለ። ሎጥ ከአብርሃም ጋር ከሄደና እንዲህ ከተባረከ በኋላ ግን፥ እኔ እርሱን ብሆን፥ ከአብርሃም ተለይቼ የትም ባልሄድሁ ነበር። ሰው የበረከቱን ሥፍራ በቀላሉ እንዳይለቅ መጠንቀቅ አለበት። ሎጥ ግን ታሪኩን ያስመዘገበው ትዳሩን በማጥፋትና ከልጆቹ ጋር ግብረ ሥጋዊ ግንኙነት ውስጥ በመውደቅ ለእስራኤል እፍረት መሆንን ነው።

ንጉሡ ዳዊት ሕዝቡና ሠራዊቱ በጦርነት ላይ እያሉ ፥ እቤቱ ጣርያ ላይ ምን አንጎራደደው? ትርፉስ ምን ሆነ? በማይሆን ጊዜ ፥ በማይገባ ሥፍራ መገኘት ለማይወደድ ውጤት ይዳርጋልና፥ዳዊት ራቁቷን የነበረችን ሴት ተመለከተ። ታሪኩን እንደምታውቁት መጨረሻው መልካም አልነበረም። ከራሱ አልፎ ለቤተሰቡና ለሐገሩ ብዙ መከራ አስከተለ። ወገኖቼ፥ዳዊት ንፁሕ ነፍስ እስከ ማጥፋት የደረሰው በዚያን ጊዜ፥ያለ ሥፍራው በመገኘቱ ከገባበት ማጥ ለማምለጥ ነበር።

አንድ ጓደኛዬ ከነቤተሰቡ ሲኒማ ቤት ገብተው የፊልሙን መጀመር ይጠባበቁ ነበር። ወዲያውም ጎረምሳ ለመምሰል ይፈልግ የነበረው ትንሹ ልጁ፥"አባቴ፥ሽንት ቤት መጠቀም አለብኝ" አለው። አባትየውም "ና ላድርስህ" አለው።ልጁ ግን ሕፃን እንዲባል ስለማይፈልግ፥"ብቻዬን መሄድ እችላለሁ" ሲል እምቢ አለና ተነሥቶ ሄደ።

ከትንሽ ጊዜ በኋላ፦እያኮረፈ ተመልሶ መጣ። አባትየውም፥ገርሞት፥"ሽንት ቤት አገኘህ?"ሲል ጠየቀው። ልጁም በኩርፊያ "አዎን" አለ። አባትየውም "ታዲያስ ተጠቀምህ?" ብሎ ሲጠይቀው፥ልጁ ቆጣ አለና፦"ሴቶች በወንዶች ሽንት ቤት ውስጥ ሞልተው ቆዩኝ" ሲል ንዴቱን ገለጠ። ነገር ግን ልጁ ራሱ ተሳስቶ የሴቶች ሽንት ቤት ገብቶ ነው እንጂ ሴቶቹ ያው በሴቶች ሽንት ቤት ነበሩ።

እንደዚህ ሕፃን፦ ያለሥፍራቸው ገብተው ሰው ሁሉ ጥፋተኛ የሚመስላቸው ወቃሽና ተቺዎች፥ እንዲሁም በማኩረፍ የተካኑ ስንት ክርስቲያኖች ይኖሩ ይሆን?

## 7. በትክክለኛው ሥፍራ መሆን አብዛኛውን የሕይወት ችግሮች ያስወግዳል

እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በመጋባት፡ በትክክለኛው ከተማ በመኖር፥ እንደ ፈቃዱ በሆነ ቤተ ክርስቲያን በማምለክና በማገልገል፥ በትክክለኛው ሥራ ላይ በመሰማራት፥ እንዲሁም ጓደኞችን እንደ እግዚአብሔር ፈቃደ በመምረጥ፦ ሰው አብዛኛውን መከራውን ማስወገድ ይችላል።

ከማጠቃለሌ በፊት፦ በትክክለኛው ሥፍራ ስለ መሆን፥ አምስት ወሳኝ የሆኑ ነገሮችን ጠቁሜ እፈጽማለሁ።

**1ኛ፦ ንስሐ መግባት።** እግዚአብሔር ሳይመራህ፥በፊትህ መልካም መስሎ የታየህን ሁሉ አድርገህ ከሆነ በጌታ ፊት ንስሐ ግባ። ከዚያም ጌታ ሥፍራህን እንዲያሳይህ በመጸለይ፥ ግልጽ ምሪት እስክታገኝ ታገሥ። እግዚአብሔርንም በመታመን የሚጠባበቁት ኃይላቸውን ያድሳሉ፤እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፤ይሮጣሉ፥ አይታክቱም፤ይሄዳሉ፥አይደክሙም፡ተብሎ እንደ ተጻፈው፦ ይሆንልሃል። የጌታም ምሪት አይዘገይም። በጊዜው የሚመጣ ምሪትም አያሳስትም። እግዚአብሔርን በመጠበቅህም ምንም የሚጎድልብህ ነገር አይኖርም፤ ክብር ለስሙ ይሁን። ስለዚህ በንስሐ ልብህን ብታስተካክልና በጸሎት ብትጠብቀው ጌታ ወደ ሥፍራህ በድንቅ ሊያደርስህ የተመነ ነው፡ ስሙ ይክበር።

**2ኛ፦ ትጉት መሆን።** ሥፍራህን በስሕተት መልቀቅህ ቢታወቅህ፦ በትኅትና ወደ መጣህበት ተመለስ። የጠፋው ልጅ ወደ ልቡ በተመለሰ ጊዜ፥ ከዚህ የተሳሳተ ሥፍራ ምን አለኝ? ልነሣና ወደ አባቴ ቤት ልሂድ እንዳለ፥ ወዲያውም በአባቱ ፊት ምሕረትና ሞገስ እንዳገኘ፥

በትኅትና ተነሥተህ ተመለስ::እንዲህም አድርገህ÷ ሰዎች መልሰው ባይቀበሉህ እንኳን÷ራስህን አዋርደህ በመመለስህ ጌታ በታማኝነቱ የተሻለ ሥፍራ ያዘጋጅልሃል:: ትኅትናህንም ቆጥሮ ካሰብኸው አብልጦ ይባርክሃል::

**3ኛ:- በዕምነት መጸለይ::** የሐዋ/ሥራ 17÷26"እርሱ የሰውን ዘር ሁሉ ከአንድ ሰው ፈጠረ፤ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩም አደረገ፤ የተወሰኑ ዘመኖችንና የሚኖሩባቸውንም ቦታዎች መበደላቸው::" ይላል:: (አዲሱ ትርጉም) አምላካችን እያንዳንዱን ሰው የፈጠረው በትክክለኛው ጊዜና ሥፍራ ነው:: የጥንቱን አገልጋዮች ለጥንቱ ዘመን÷ እኛን ደግሞ ለዚህ ትውልድ አገልግሎት መድቦ ፈጥሮናል:: ስለዚህ:- አባት ሆይ! ፈቃድህን የማገለግልበትን ሥፍራዬን አሳየኝ ብሎ በዕምነት መጸለይ ጌታን ደስ ይለዋል::

**4ኛ:- እግዚአብሔር ምሪትን ስንለምነው ሊመራን ዝግጁ መሆኑን ርግጠኛ ሆኖ መጸለይ**

ጸሎትህን ለአምላክህ ካቀረብህ በኋላ ወዲያውኑ መልስህን ለመቀበል ተዘጋጅ:: ጌታ መልስህን የሚያመጣበትን ጊዜ ስለማታውቅ÷ በንቃት ተጠባበቅ:: ለምሳሌ ቃሉን ስታነብብ ወይም ስትሰማ÷ በመንፈስ ቅዱስ÷ በውስጣዊ ሰላምና በእግዚአብሔር ሰዎች አማካይነት ሊመልስልህ ስለሚችል÷ በዕምነት ነቅተህ መጠባበቅ አለብህ:: በዚህ አጋጣሚ አንድ ነገር ላረጋግጥልህ:- እግዚአብሔር በማይረባ አገልግሎት÷ትዳር ሆነ መሥሪያ ቤት ውስጥ ጥሎ አልዘጋብህም:: እርሱስ ለዘላለም የሚያስለቅስ ጨካኝ አምላክ አይደለም:: ስለዚህ ከሚያስለቅስህ ሁኔታ ለመውጣት ውሳኔ ማድረግ ያለብህ አንተው ራስህ ነህ:: ጌታ ግን ጻድቃን በዕምነት ወደ እርሱ ሲጸልዩ ሁኔታቸውን በድንቅ በመለወጥ የታወቀ አምላክ ነው፡ ክብር ለስሙ ይሁን::

በዕድሜአችን ውስጥ ፈጽሞ መቋረጥ የሌለባቸው ወዳጅነቶች አሉ:: አንዳንድ ወንድሞችና እህቶች ለዕድሜ ልክ የተሰጡን÷ለአገልግሎታችን የሚረዱን የጌታ ስጦታዎች ስለ ሆኑ÷ በጥንቃቄ መጠበቅ አለባቸው:: አንዳንድ ወዳጆች ደግሞ እጃችንን ይዘው ወደ እግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ለመግባት የሚረዱን የጌታ መሣሪያዎች ናቸው:: ስለዚህ በጌታ ከተዋወቅናቸው ሰዎች አንዳንዶቹን እስከ ዕለተ ሞታችን ድረስ ወዳጅነታቸውን መጣል የለብንም::

ስለ ራሴ ዕውነተኛ ታሪክ ልንገራችሁ፡ ከአሥራ አምስት ዓመት በፊት÷ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ታላቅ የፈውስ አገልግሎት በተደረገበት ጊዜ÷ከቤኒ ሂን ጋር ደቡብ አፍሪካ ሄጄ ነበር:: እኔ በአሰተዳደጌ ጥምቀት ላይ ከሚያተኩር ቤተ ክርስቲያን ነበርሁ:: ነገር ግን በዚያን ሰሞን በመንፈስቅዱስ ስለተጠመቅሁ የመንፈስ ቅዱስን አሠራር ለማየትና ለመማር ነበር የሄድሁት:: ወጪዬን በሙሉ ራሴ ችዬ በሄድሁበት በዚያን ቦታ ከአንድ ሰው ጋር ተዋወቅሁ::

ይህም ሰው ቤኒ ሂንን ያስተናግድ የነበረው÷ሬይ መኮሊ የተባለው የሬማ ባይብል ቤተ ክርስቲያን መጋቢ የነበረው ነው:: ሃያ ሺህ የሚሆኑ ሰዎችን የሚያገለግል÷ ሁሉን ዘር ያቀፈ÷በቴፕና በቪዲዮ አውሮጳን የሚደርስ÷ የተሳካ ታላቅ አገልግሎት ነው::ያን በመሰለ ሥፍራ ነው፡ሸራ ጫማዬን አድርጌ÷ ጂንሴን ለብሼ÷ ያለ ምንም የአለባበስ ሥርዓት የነበርሁት:: በዚያን ጊዜ መድረኩ ላይ የነበሩት:- ታላላቅና ዝነኞች ሰዎች ነበሩ:: ከቱልሳ የመጡ የዕምነትና የብልጽግና አስተማሪዎች በዓለም ላይ ምርጥ የተባሉትን ልብሶች የተኀናጸፉ÷ ጫማዎቻቸው እጹብ ድንቅ የሚያሰኙ÷የወርቅ ሰዓታቸው የሚያብለጨልጭ ነበሩ:: እኔ ግን ለማየት ብቻ ስለ ሄድሁ ኮት እንኳ አልነበረኝም::

ይህ በእንዲህ እያለ ፓስተር ሬይ ከቤኒ ሂን ጋር እቤቱ ምሣ ጋበዘኝ:: በቤኒ ምክንያት ተጋበዝሁ እንጂ ሬይ አያውቀኝም ነበር:: በምሣም ላይ ሳለን÷መንፈሴ ከፓስተር ሬይ መንፈስ ጋር ተጋጠመ:: ምክንያቱን ባላውቅም ልቡ በእኔ÷ የእኔም በእርሱ ላይ በጌታ ፍቅር አረፈ::

በነጋታውም ፓስተር ሬይ ሆቴል ደውለና:- ሐሙስ ከቀኑ በስምንት ሰዓት ባለን ዝግጅት ላይ አገልግለን አለኝ::እኔም በድንጋጤ እየተንተባተብሁ እሺ ብየ ተቀበልሁ:: ትንሽ ቆይቼ ግን ፍርሐት አስቸገረኝ:: ምክንያቱም በዚያ ስብሰባ ላይ ቢያንስ ስድስት ሺህ ሰዎች ይኖራሉ:: ከዚያም በላይ አለባበሴ ያሳፍረኝ ነበር:: ሆኖም መጨረሻ ላይ ውሳኔ አደረግሁ::

ጌታንም እንዲህ እያልሁ ማነጋገር ጀመርሁ:: ጌታ ሆይ÷ ሳይታወቀኝ ከሕይወቴ ዓላማ ጋር እያጋጠምኸኝ ይሆናል፤ ስለዚህ ይህ ለመነሻዬ ያዘጋጀኸው ዕድል መሆኑን እንዳውቅ፤በዚህ ልፈትን አልሁ:: ኮትና ክራባት ሳልለብስ ሸራ ጫማ አድርጌ እሰብካለሁ:: በሕዝብህና በአንተ ፊት ሞገስ ካገኘሁ አንተ እንዳመጣኸኝ ምልክት ይሁነኝ:: ካልሆነ ግን አንተ ሳትጠራኝ መጥቼ ጥሩ ነገር ስላለማመድኸኝ አመስግኜ ወደ ቤቴ እመለሳለሁ አልሁ፡

ከዚያም ሰዓቱ ሲደርስ:- በቆራጥነት÷ ጂንሴን ለብሼ በሸራ ጫማ በዚያ ታላቅ ሕዝብ ፊት ቆሜ መስበክ ጀመርሁ:: ሦስት ደቂቃ ሳይሞላ የጌታዬ ጸጋ መፍሰስ ጀመረ:: ቃሉ ተገለጠ÷ሕዝቡ ይባረክ ጀመር÷እኔም በእርግጥ ያቺ ቀን፡ የሕይወቴ ዓላማ መገለጫ ቀጠሮ መሆኗን አውቄ ተመለስሁ:: ከዚያም ወንድም ጋር ያገኘሁትን ወዳጅነት እስከ ዛሬ ድረስ በጥንቃቄ ይዤዋለሁ:: እይዘውማለሁ:: በፓስተር ሬይ መኮሌ ቤተክርስቲያን በተቀረጹ ቴፖችና ቪዲዮዎች አማካይነት አገልግሎቴ በዓለም ሁሉ ሊታወቅ ቻለ::ያም ለእኔ÷የጌታ ልዩ ረድኤት መሆኑ ይታወቀኛል:: ስለዚህ የፓስተር ሬይን ወዳጅነት በምቹና በማይመችም ሁኔታ ሁሉ በጥንቃቄ እጠብቀዋለሁ:: የቱንም ያክል ስጦታና ጸጋ ቢኖርህም እንኳ ያለ ጥሩ ወዳጆች ርዳታ ወደታሰበልህ ሥፍራህ መድረስ አትችልም:: ስለዚህ ጌታ የሚያገናኝህን ወዳጆች ለዘለቄታው በማስተዋል ጠብቅ::

**5ኛ:- ሥፍራህን ስትይዝ ሌሎች ሥፍራቸውን እንዲያገኙ ለመርዳት ትጋ**

ጌታ ካሰበልህ ሥፍራ ደርሰህ÷ሰላምና ርካታ አግኝተህ ልብህ ሲያርፍ:- ሌሎች ደግሞ የአንተ ርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው አትርሳ:: ትዕቢተኛውንና አመጸኛውን ወይም "እግዚአብሔር ተናግሮኛል" ምክር አልቀበልም ባዮችን ማንም ሊረዳ አይችልም:: ራዕያቸውን ለመሪያቸው ገልጸው÷ ጊዜ ወስደው ጸልየውበትና መክረውበት ሳይሆን÷ያሰኛቸውን ወስነው፡ ባርከህ ስደደኝ በማለት የሚመጡብህን መርዳት አትችልም:: መከልከል ባትችልም ባርከህ የመስደድም ግዴታ የለብህም:: ነገር ግን ጌታ ያዘጋጃቸው ደጋፊና ኣሳዳጊ የሚያስፈልጋቸው ትኍታን ታዳጊዎች እንዳሉ አትዘንጋ::

በመጨረሻ:-በጌታ ፍቅር የምመክርህን ቁም ነገር አስተውልልኝ:: ሥፍራህን ዕወቅ:: ወደ ሥፍራህም ፍጠን፤አትልቀቀውም:: በምንም ምክንያት ሥፍራህን ለቅቀህ ከሆነ÷ንስሐ ገብተህ በቶሎ ተመለስ:: በዚያም ጽና ! ይከናወንልሃልም:: አንቺም::

ይህንን አገለግሎት መደገፍ ጌታ ቢያሳስባችሁ ወይም የአድራሻ ለውጥ ብታደርጉ በሚከተለው አድራሻ ጻፉልን::

God's Love
P.O.Box 6734
Lee's Summit, MO 64064
USA

ወይም በኢ- ደብዳቤ

glnlm@ethiogodslove.org

## መልካም አዲስ ዓመት

ውድ አንባቢዎቻችን:- በአዲሱ ዓመት አዲስ ተስፋና አዲስ ጸጋ እንዲበዛላችሁ ጸሎታችን ነው። ያልተመለሱ ጸሎቶቻችሁ በዚህ ዓመት ይመለሱ። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፤ አሜን።

ይህንን የደብዳቤ መልዕክት:- በ1999 ዓም (እአአ) በትንሹ ጀመርን። እያደገን መጥተን፥ በ2003 አጋማሽ ገደማ ደግሞ ይህንኑ አገልግሎት በዌብ ገጽ ማቅረብ ጀመርን።

በአሁኑ ጊዜ በዌብና በደብዳቤ በዓለም አቀፍ በተበተኑት ወገኖቻችን የሚነበበውን ደብዳቤአችንን በተሻለ አኳኋን ለመቀጠል የሚበጅ ሆኖ ስላገኘነው፥የሚከተለውን ለውጥ አድርገናል።

ይኸውም÷ ከእግዚአብሔር ፍቅር ደብዳቤአችን:- እንደ ነበረው በየወሩ መሆኑ ቀርቶ÷በየሦስት ወሩ አንዴ ይወጣል:: የገጹን ብዛት ጸጋው እንደ በዛልን ከሁለት ወደ አራት ከፍ ልናደርግ በዕምነት ወስነናል::

የዌብ ገጽ አገልግሎታችንን የበለጠ ጠቃሚ በሚሆንበት አኳኋን ለማሻሻል እየጸለይንና እየመከርን ነው። ወገኖቻችን በጸሎታችሁና ጌታ በሚያሳያችሁ ሁሉ ድጋፋችሁን እንድትቀጥሉ እንጠይቃችኋለን።

እስካሁን በሚቻላችሁ ሁሉ በታማኝነት የደገፋችሁንን ሁሉ ጌታ ብድራታችሁን በእጥፍ ይመልስላችሁ እያልን ልባዊ ምሥጋናችንን እናቀርባለን። ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ፡

በአፍሪካ ያሉትን አንባቢዎቻችንን እስፖንሰር የምታደርጉ:-ድጋፋችሁን በአዲሱ ዓመት እንድታድሱ እና ሳስባችኋለን:: ጌታ ይባርካችሁ::

Enjoy our web page ministry @

www.ethioGodslove.org

By the grace of God, this page provides visiters with 36 Amharic Gospel News-letters and 22 best gospel songs. God bless.

**ብርክቲ አፈወርቅ:-** እንድናፋልግሽ የጠየቅሽንን ወንድሞችሽን ጌታ ረድቶን ስላገኘናቸው÷ በተቻለ ፍጥነት በዚህ ኢሜይል እንድትጽፊልን እናሳስባለን::

glnlm@ethiogodslove.org

ብሩክ አዲስ ዓመት ምሕረት

ኢየሱስ ጌታ ነው::

ጌታ ይባርካችሁ::